# ዜና አመዝኤ



የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ፤ ቅፅ 12 ቁጥር 7 ታህሳስ/ጥር 1998

# 2.6 ሚሊዮን ሕዝብ የአስቸኳይ ጊዜ ምግብ ዕርዳታ ይፈልጋል

እ.ኤ.አ በ2006 ዓ.ም በሀገሪቱ የተለያዩ ክልሎች የአስቸኳይ ጊዜ ምግብ ዕርዳታ ለሚያስፈልጋቸው 2.6 ሚሊዮን ሰዎች በጠቅላላው 339 ሺህ 090 ሜ/ቶን የምግብ ዕርዳታ እና ምግብ ነክ ላልሆኑ የአስቸኳይ ጊዜ ተዛማጅ ዕርዳታዎች ደግሞ 123 ሚሊዮን 334 ሺህ 234 የአሜሪካ ዶላር እንደሚያስፈልግ ተገለፀ።



ይኽ የተገለፀው የኢትዮጵያ መንግሥት ፣ የተባበሩት መንግሥታት እና የረድኤት ድርጅቶች በጋራ ያዘጋጁት እ.ኤ.አ የ2006 ዓ.ም ሰብዓዊ የአስቸኳይ ዕርዳታ ሰነድ ጥር 15 ቀን 1998 ዓ.ም ይፋ በተደረገበት ወቅት ነው። የዕርዳታ ጥያቄው ለለጋሽ ሀገራት አምባሳደሮችና ተወካዮች ፣ ለረድኤት ድርጅቶችና ለሚመለከታቸው አካላት በቀረበበት ወቅት የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ሲሞን መቻለ እንደተናገሩት ባለፈው ዓመት ሰብል አብቃይ በሆኑት የሀገሪቱ ክፍሎች የነበረው የዝናብ ሁኔታ በመጠንና በሥርጭት ጥሩ የነበረ በመሆኑ ፣ ከምግብ ዋስትና እና ድህነት ቅነሳ ጋር በተያያዘ የተሻሉ ሥራዎች በመሠራታቸው ፣ እንዲሁም አስቸኳይ ዕርዳታ የሚያስፈልገውን ሕዝብ ለመለየት የተሻለ የአጠናን ዘዴ ተግባራዊ በመደረጉ ሳቢያ በዚህ ዓመት በሀገሪቱ አስቸኳይ የምግብ ዕርዳታ የሚያስፈልገው ሕዝብ ካለፉት ዓመታት ጋር ሲነፃፀር በእጅጉ ሊቀንስ ችሏል።

አስቸኳይ የምግብ ዕርዳታ ያስፈልገዋል ተብሎ ከተያዘው ጠቅላላ ሕዝብ 67 በመቶው በሱማሌ ክልል ፣ በኦሮሚያ ክልል ቦረና ዞንና በአፋር ክልል እንደሚገኝ የጠቀሱት አቶ ሲሞን ይኽም ሊሆን የቻለው በሱማሌ ክልልና በኦሮሚያ ክልል ቦረና ዞን ባለፈው ጥቅምትና ህዳር ይጠበቅ የነበረው የወቅቱ ዝናብ ሳይጥል በመቅረቱ እና በዚህም ሳቢያ ከፍተኛ የሆነ የግጦሽና የውሃ እጥረት በመከሰቱ ፣ እንዲሁም በአፋር ክልል ባለፈው ክረምት የዝናቡ መጠን አነስተኛ ስለነበረ ያለው ውህና ግጦሽ ለረጅም ጊዜ ሊቆይ ባለመቻሉ ነው ብለዋል። ቀሪው 30% ዕርዳታ ፈላጊ በሰብል አብቃይ የሀገሪቱ ክፍሎች እንደሚገኝ ዋና ዳይሬክተሩ አመልክተው ለመጀመሪያ ጊዜ የትግራይና የሀረሪ ክልሎች ከአስቸኳይ ዕርዳታ ፍላጎት ውጭ መሆናቸውንና በሴፍቲኔት ኘሮግራም መታቀፋቸውን አስታውቀዋል። በማያያዝም በነዚህ ምክንያቶች ለምግብ እጥረት ለተጋለጡ አርብቶ አደሮችና በሌሎችም የሀገሪቱ አንዳንድ አካባቢዎች አስቸኳይ የምግብ ዕርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች በጠቅላላው 339 ሺህ 090 ቶን ምግብ የሚያስፈልግ ቢሆንም ከዚህ

## በዚህ እትም ውስጥ

አዲስ የተሾሙት የአመዝኤ ም/ዋና ዳይ ክተርልዩ ልዩ የሥራ ዘርፎችን ጎበኙ
ገጽ 3

ሀያ ሁለት የሥርዓተ ምግብ ጥናቶች ተካሄዱ
ገጽ 4

በሱማሌ ክልል የተከሰተውን ድርቅ ለመቋቋም ተገቢው እርምጃ እየተወሰደ ነው
ገጽ 4

በበጀት ዓመቱ ከ400 በላይ ለሚሆኑ ባለሙያዎች ሥልጠና ተሰጠ
ገጽ 5

በብር 245.6 ሺህ እህልና ቁሳቁስ ከአገር ውስጥ ግዥ ተከናውኗል
ገጽ 6

የናሙና የጥናት ኘሮጀክቱ ነባሩን የአደጋ ተጋላጭነት ደረጃ አጠናን ስልት ለማሻሻል ያስችላል ተባለ
ገጽ 6

በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ
ስልክ. 529259
529262
ጠ.ሳ.ቁ 5686
ድረገጽ፧ www.dppc.gov.et

ዜና አመዝኮ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲና ተባባሪዎቹን የሚያካሂዷቸውን የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት እንቅስቃሴዎችንና ሌሎች ተጎዳኝ ተግባራትን የሚዘግብ ወርሃዊ ልሳን ነው

ውስጥ 238 ሺህ 26 ቶን በ2005 ቃል ከተገባውና በክምችት ካለው ወደዚህኛው ዓመት የተላለፈ በመሆኑ ለዚህ ዓመት የሚኖረው የተጣራ የምግብ ዕርዳታ ፍላጎት 101 ሺህ 066 ቶን መሆኑን ገልፀዋል።

ከዚህም በተጨማሪ ጤናና ሥነምግብ ፣ ውሀ እና የአካባቢ ንጽህና ፣ የግብርና ግብአቶች ፣ የአደጋ ምላሽ አቅም ግንባታና አጠቃላይ የማስተባበር ሥራና ለመሳሰሉት ምግብ ነክ ያልሆኑ የአስቸኳይ ጊዜ ተዛማጅ ዕርዳታዎች ማስፈጸሚያ 123 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር እንደሚያስፈልግ ተመልክቷል።

ጤናና ሥነምግብ ፣ ውሀ እና የአካባቢ ንጽህና ፣ የግብርና ግብአቶች ፣ የአደጋ ምላሽ አቅም ግንባታና አጠቃላይ የማስተባበር ሥራና ለመሳሰሉት ምግብ ነክ ያልሆኑ የአስቸኳይ ጊዜ ተዛማጅ ዕርዳታዎች ማስፈጸሚያ 123 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር እንደሚያስፈልግ ተመልክቷል።

ባሳለፍነው የፈረንጆች 2005 ዓ.ም የተባበሩት መንግሥታት የተለያዩ ዘርፎች ፣ ለጋሽ ሀገራትና የረድኤት ድርጅቶች ከመንግሥት ጎን በመቆም አስቸኳይ የምግብ ዕርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች አስፈላጊውን ወቅታዊ የሆነ የዕርዳታ እጅ ለመዘርጋት ባደረጉት ያላሰለሰ ጥረት የበርካታ ወገኖችን ሕይወት ለመታደግ መቻሉን የጠቀሱት ዋና ዳይሬክተሩ በተመሳሳይ ሁኔታ ከፊታችን የተደቀነውን ሕይወት የማዳን ሥራ እንደተለመደው በተባበረ ጥረት በአሸናፊነት እንደምንወጣው እምነቴ ነው ብለዋል። አያይዘውም የዓለም አቀፉ ማህበረሰብና የረድኤት ድርጅቶች አስቸኳይ ዕርዳታ ለሚያስፈልጋቸው በወቅቱ በማቅረብ ረገድ ለሚያደርጉት የሁልጊዜ ትብብር በመንግሥትና በተረጂ ወገኖች ስም ከልብ የመነጨ ምስጋና አቀርባለሁ ብለዋል።

በተባበሩት መንግሥታት ህፃናት መርጃ ድርጅት የኢትዮጵያ ተጠሪና በኢትዮጵያ የተመድ ሰብአዊ ጉዳዮች አስተባባሪ ተወካይ ሚ/ር ቢዮረን ሊንኪዊቪስት በበኩላቸው በሀገሪቱ የነበረው ያለፈው ዓመት የአየር ሁኔታ በአብዛኛው ለሰብል ምርት ምቹ ስለነበረና ከዚህም ጎን ለጎን በምግብ ዋስትና ኘሮግራሙ ረገድ ጠንካራ ሥራዎች በመሰራታቸው የአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ ፈላጊው ሕዝብ ቁጥር ካለፉት ዓመታት ጋር ሲነፃፀር በእጅጉ መቀነሱ ለሁላችንም የሚያስደስት ነው ካሉ በኋላ የምግብ ዋስትና ችግሩ በዘላቂነት በሚታይባቸው አካባቢዎች የሚገኘውን ሕዝብ በሴፍቲኔት ኘሮግራሙ በስፉት ለማካተት መታሰቡም ለአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ ፈላጊው ቁጥር መቀነስ አስተዋጽኦ አድርጓል ብለዋል።

በዚህ ሳቢያ የአስቸኳይ ምግብ ዕርዳታ ፍላጎቱ ጫና መቀነስ እንድንዘናጋ የሚያደርገን ሳይሆን እንደ ጤናና ሥነ ምግብ ፣ ውሀና የአካባቢ ንጽህና ፣ ግብርና ፣ የአደጋ ምላሽ አቅም ግንባታና በመሳሰሉት ምግብ ነክ ባልሆኑ የአስቸኳይ ጊዜ ተዛማጅ ዕርዳታዎች ጥያቄ ካለፉት ዓመታት ጋር ሲነፃፀር ከፍ ያለ መሆኑን በማጤን ይበልጥ ትኩረት ልንሰጥ እንደሚገባን በግልጽ ያመለክታል ብለዋል።

በመሆኑም ዓለም አቀፉ ለጋሽ ማህበረሰብ በኢትዮጵያ የሚታየውን የምግብ እጥረት ችግር ለማቃለል የልግስና እጁን በወቅቱ መዘርጋት እንደሚጠበቅበት አሳስበዋል። በተጨማሪም ባለፉት ዓመታት ተከስተው ከነበሩ የድርቅ አደጋዎች ጋር በተያያዘ የሚከሰቱ የጤና ፣ የንፁህ ውሀ አቅርቦት፣ ሥነ ምግብ እና የመሳሰሉትን ችግሮች ሙሉ በሙሉ ለመቅረፍ የሚያስችል አስፈላጊውን ሰብአዊ ዕርዳታ በወቅቱ ለጋሾች እንዲያቀርቡ ጠይቀዋል።

በመጨረሻም በቀረበው የዕርዳታ ጥያቄ ዙሪያ ጥሪ ከቀረበላቸው ተሰብሳቢዎች አስተያየቶችና ጥያቄዎች ተሰንዝረው ሰፋ ያለ ውይይት የተደረገ መሆኑ ታውቋል።

# አዲስ የተሾሙት የአመዝኤ ም/ዋና ዳይሬክተር ልዩ ልዩ የሥራ ዘርፎችን ጎበኙ



አቶ ገብረመድህን በላይ የአመዝኤ ም/ዋና ዳይሬክተር ሆነው ከመሾማቸው በፊት ከመጋቢት 1996 እስከ ህዳር 1998 የቱሪዝም ኮሚሽን ም/ኮሚሽነር፣ ከጥቅምት 1994 እስከ የካቲት 1996 የግብርና ሚኒስቴር ም/ሚኒስትር፣ ከጥር 1986 እስከ መስከረም 1994 በግብርና ሚኒስቴር የኘላንና ኘሮግራም መምሪያ ኃላፊ በመሆን ከ12 ዓመት በላይ በከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊነት ቦታዎች ላይ ሲሰሩ ቆይተዋል።

የፌዴራል አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ /አመዝኤ/ ም/ዋና ዳይሬክተር በመሆን ከታህሳስ 17 ቀን 1998 ዓ.ም ጀምሮ በጠቅላይ ሚኒስትር የተሾሙት አቶ ገብረመድህን በላይ የመ/ቤቱን የሥራ ዘርፎች ተዘዋውረው በመጎብኘት፣ ከመምሪያ፣ አገልግሎትና በየደረጃው ከሚገኙ የሥራ ኃላፊዎች ጋር ትውውቅና ሠፊ ውይይት አድርገዋል።

ም/ዋና ዳይሬክተር ገብረመድህን በላይ ከጥር 3 ቀን 1998 ዓ.ም ጀምሮ የኤጀንሲውን የሥራ ዘርፎችና፣ ኤጀንሲው የሚያስተዳድራቸውን የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደርና የብሔራዊ አደጋ



መከላከልና ዝግጁነት ፈንድ ጽ/ቤት፣ እንዲሁም የድሬደዋ የኮምቦልቻ ማዕከላዊ መጋዘኖችን በጎበኙበት ወቅት ከኃላፊዎች ስለሥራ ዘርፎቻቸው አደረጃጀት፣ ተግባርና ኃላፊነት፣ የውስጥና የውጭ ግንኙነቶችን አስመልክቶ ሰፊ ማብራሪያ ተደርጎላቸዋል።

በጉብኝቱ ወቅት ም/ዋና ዳይሬክተሩ እንደተናገሩት የሥራ ጉብኝቱና የትውውቅ ኘሮግራሙ ዋነኛ ዓላማ ስለእያንዳንዱ የሥራ ዘርፍ አሠራር አጠቃላይ ግንዛቤ ለመጨበጥና ከሚመለከታቸው ኃላፊዎች ጋር በቅርበት በመነጋገር ለቀጣይ ሥራ ጠንካራ መሠረት የሚጥል ነው ብለዋል። አያይዘውም በቀጣይ የኤጀንሲውንና በምግብ ክምችት አስተዳደርና የአመዝ ፈንድ ጽሕፈት ቤት ዓላማዎች ስኬት በሚደረገው የተቀናጀ እንቅስቃሴ ውስጥ የበኩላቸውን ድርሻ ለመወጣትና በቅርበት ለመሥራት መድረክ ለመፍጠር እንደሆነም አመልክተዋል።

በኤጀንሲው በሰው ኃይልና በዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ረገድ የሚታየው ሁኔታ አበረታች መሆኑን የጠቀሱት ም/ዋና ዳይሬክተሩ ይህም ኤጀንሲው የአደጋ ሰለባዎችን ሕይወት ለመታደግ ለሚያደርገው እንቅስቃሴ ስኬታማነትም ሁነኛ መሠረቱ እንደሆነው በቅርብ ለመገንዘብ መቻላቸውንም ገልፀዋል።

አቶ ገብረመድህን በላይ በመንግሥት መ/ቤቶች በተለያዩ የኃላፊነት ደረጃዎች በሰሩባቸው 28 ዓመታት ውስጥ የአመዝኤ ም/ዋና ዳይሬክተር ሆነው ከመሾማቸው በፊት ከመጋቢት 1996 እስከ ህዳር 1998 የቱሪዝም ኮሚሽን ም/ኮሚሽነር፣ ከጥቅምት 1994 እስከ የካቲት 1996 የግብርና ሚኒስቴር ም/ሚኒስትር፣ ከጥር 1986 እስከ መስከረም 1994 በግብርና ሚኒስቴር የኘላንና ኘሮግራም መምሪያ ኃላፊ በመሆን ከ12 ዓመት በላይ በከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊነት ቦታዎች ላይ ሲሰሩ ቆይተዋል።

አቶ ገ/መድህን በላይ ኔዘርላንድ ሄግ ከሚገኘው ኢንስቲትዩት ኦፍ ሶሻል ስተዲስ በዲቬሎኘመንት ስተዲስ በግብርናና ገጠር ልማት መስክ በ1977 ዓ.ም የኤም.ኤስ.ሲ ዲግሪያቸውን፣ በኘሮጀክት ኘላንና ትንተና በ1975 ዓ.ም የድህረ ምረቃ ዲኘሎማ አግኝተዋል። በተጨማሪም ከቀድሞው ዓለማያ እርሻ ኮሌጅ የአሁኑ ዓለማያ ዩኒቨርስቲ በ1970 ዓ.ም የመጀመሪያ ድግሪያቸውን በግብርና ኤኮኖሚክስ ማግኘታቸውም ታውቋል።

# ሀያ ሁለት የሥርዓተ ምግብ ጥናቶች ተካሄዱ



ከሰኔ 1997 ዓ.ም እስከ ጥቅምት 1998 ዓ.ም ድረስ ባሉት አምስት ወራት ውስጥ በኤጀንሲውና በዘጠኝ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አማካይነት በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ፣ በኦሮሚያ ፣ በአማራ ፣ እና በአፋር ክልሎች በሚገኙ 19 ወረዳዎች 22 የሥርዓተ ምግብ ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡

በድርቅና ተዛማጅ አደጋዎች አማካይነት የምግብ እጥረት በተከሰተባቸው አካባቢዎች በይበልጥ ተጎጂ የሆኑ ህፃናቶችና እናቶችን ለመታደግ የሚያስችሉ ሀያ ሁለት የሥርዓተ-ምግብ ጥናቶች በተለያዩ መንግሥታዊ ያልሆኑ የረድኤት ድርጅቶችና በአመዝኤ አማካይነት መካሄዳቸው ተገለፀ፡፡

በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ መምሪያ የአደጋ አካባቢዎች ጥናት ቡድን የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ከሰኔ 1997 ዓ.ም እስከ ጥቅምት 1998 ዓ.ም ድረስ ባሉት አምስት ወራት ውስጥ በኤጀንሲውና በዘጠኝ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አማካይነት በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ፣ በኦሮሚያ ፣ በአማራ ፣ እና በአፋር ክልሎች በሚገኙ 19 ወረዳዎች 22 የሥርዓተ ምግብ ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡

ጥናቶቹ የተካሄዱት በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በአዋሳ ዙሪያ ፣ ስልጢ ፣ቁጫ ፣ ቦሎሶ ሶሬ፣ ዳሞት ጋሌ እና ዳሌ ወረዳዎች፣ በኦሮሚያ ክልል በዳሮለቡ ፣ ዶዶታ ሲ ፣ ዝዋይ ዱግዳ ፣ ቁኒ ፣ ኩርፋጨሌ ፣ በደኖ እና ግራዋ ወረዳዎች ፣ በአማራ ክልል በቃሉ ፣ በደሴ ዙሪያ ፣ ደሀና እና ሰቆጣ ወረዳዎች እንዲሁም በአፋር ክልል በአባላ እና በራህሌ ወረዳዎች ነው፡፡ በተጠቀሱት ክልሎች የረድኤት ሥራ በሚያከናውኑባቸው ወረዳዎች ጥናቶቹን ካካሄዱት ዋና ዋና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ውስጥ ጎል ኢትዮጵያ ፣ የአሜሪካና የእንግሊዝ ህፃናት መርጃ ድርጅቶች ፣ ኮንሰርን ኢትዮጵያ ፣ መርሊን ፣ ኬር ኢትዮጵያ እና አመዝኤ እንደሁኔታው በጋራና በተናጠል የሚገኙበት መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ቡድኑ እንደገለፀው ለዚሁ ተግባር የአስቸኳይ ጊዜ ሥርዓተ ምግብ ማስተባበሪያ ክፍል በድርቅ እና ተዛማጅ አደጋዎች አማካይነት የምግብ እጥረት በሚከሰትባቸው አካበቢዎች በምግብ እጥረቱ ይበልጥ ተጎጂ የሚሆኑትን ህፃናትና እናቶችን ለመታደግ የሚያስችሉ ፈጣን እርምጃዎችን ለመውሰድ ይቻል ዘንድ ወቅታዊ ጥናቶች የማካሄድ እና የመፍትሔ ሀሳብ የማቅረብ ሥራዎችን እንዲያስተባብር በአመዝኤ እና በተባበሩት መንግሥታት የህፃናት መርጃ ድርጅት /ዩኒሴፍ/ ትብብር ከተቋቋመ ወዲህ ያከናወናቸው ተግባራት ውጤታማ ናቸው፡፡

የማስተባበሪያ ክፍሉ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ በርካታ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችንና የተመድ አካላትን በማስተባበርና በማሳተፍ በተለያዩ ክልሎች ለምግብ እጥረት የተጋለጡ ህፃናትንና እናቶችን ለመታደግ የሚያስችሉ በርካታ ተግባራትን ያከናወነ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ ሀገር አቀፍ የሥርዓተ ምግብ መረጃዎችን ለማደራጀት መቻሉ በዋነኛነት የሚጠቀስ ነው፡፡ የአስቸኳይ ጊዜ ሥርዓተ ምግብ ጥናቶች በክልልና በወረዳ ደረጃ በሚገኙ ባለሙያዎች እንዲካሄዱ እና መረጃዎቹም በክልል ደረጃ እንዲደራጁ ለማስቻል በሁሉም ክልሎች እየተካሄዱ ያሉት የሥልጠናና የተለያዩ የአቅም ግንባታ ጅምሮችም አበረታችና ተስፋ ሰጭ መሆናቸውን ከቡድኑ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

# በሱማሌ ክልል የተከሰተውን ድርቅ ለመቋቋም ተገቢው እርምጃ እየተወሰደ ነው

*በታህሳስ ወር ከ133 ሺህ ኩንታል በላይ የምግብ ዕርዳታ ተከፋፍሏል*

የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ /አመዝኤ/ በሱማሌ ክልል በተራዘመው ደረቅ የአየር ጠባይና ወቅታዊ ዝናብ እጥረት ምክንያት በአርብቶ አደሩ አብዛኛዎቹ አካባቢዎች ግጦሽና ውሃ በመጥፋቱ ሳቢያ ለምግብ እጥረት ለተጋለጡ ወገኖች የምግብ ዕርዳታ በመላክ በሕዝብ ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ተገቢውን እርምጃ በመውሰድ ላይ ይገኛል፡፡ በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ እና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች አማካይነት



በአመዝኤ እና መያዶች ለክልሉ ተጎጂዎች ለታህሳስ ወር ከቀረበው 133 ሺህ 539 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ ውስጥ እህል 112 ሺህ 441 ኩንታል፣ የምግብ ዘይት 2 ሺህ 639 ኩንታል ፣ አልሚ የምግብ 7 ሺህ 192 ኩንታል እና ጥራጥሬ 11 ሺህ 267 ኩንታል እንደሆነም ታውቋል።

የአስቸኳይ የምግብ ዕርዳታ ለሚያስፈልጋቸው በክልሉ ዘጠኝ ዞኖች ለሚገኙ ከ789 ሺህ በላይ ተጎጂ ወገኖች በተጠናቀቀው ታህሳስ ወር 1998 ዓ.ም 133 ሺህ 539 ኩንታል ምግብ ተመድቦ ከዚሁ ለወሩ ከተከፋፈለው የምግብ ዕርዳታ ውስጥ 102 ሺህ 593 ኩንታል በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ መመደቡና ቀሪው 30 ሺህ 946 ኩንታል ደግሞ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች አማካይነት የቀረበ መሆኑ ታውቋል። በተያያዘም በአመዝኤ እና መያዶች ለክልሉ ተጎጂዎች ለታህሳስ ወር ከቀረበው 133 ሺህ 539 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ ውስጥ እህል 112 ሺህ 441 ኩንታል፣ የምግብ ዘይት 2 ሺህ 639 ኩንታል ፣ አልሚ የምግብ 7 ሺህ 192 ኩንታል እና ጥራጥሬ 11 ሺህ 267 ኩንታል እንደሆነም ታውቋል።

በክልሉ የተከሰተው የምግብ እጥረት እየሰፋና በርካታ ወገኖችን ለተረጂነት እየዳረገ ከመምጣቱ አኳያ መንግሥት የችግሩን አሳሳቢነት በማጤን በአሁኑ ጊዜ ለክልሉ ልዩ ትኩረት በመስጠቱ የአስቸኳይ ጊዜ ምግብ ዕርዳታ አቅርቦቱንም ከታህሳስ ወር ከተመደበው በእጥፍ በማሳደግ የተጠናከረ እርምጃ በመወሰድ ላይ ይገኛል። በዚሁ መሠረት ለጥር ወር በጠቅላላው 281 ሺህ 001.1 ኩንታል በአመዝኤ እና በመያዶች ተመድቦ ከግማሽ በላይ መጓጓዙና ቀሪውም በአጭር ጊዜ ውስጥ እንደሚደርስ ታውቋል። ከዚሁ ለወሩ ከተመደበው ጠቅላላ የምግብ ዕርዳታ ውስጥ 231 ሺህ 573 ኩንታል እህል ፣ 2 ሺህ 388.7 ኩንታል ዘይት ፣ 24 ሺህ 120 ኩንታል አልሚ ምግብ ፣ 22 ሺህ 969.4 ኩንታል ጥራጥ መሆኑ የተገኘው መረጃ አመልክቷል።

በተመሳሳይ መልኩም በኦሮሚያ ክልል ቦረና ዞን ለሚገኙ ተጎጂዎች በጥር ወር በጠቅላላው 28 ሺህ 790 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ ተመድቧል። ከዚሁ ለቦረና ዞን ከተመደበው የምግብ ዕርዳታ ውስጥም 23 ሺህ 250 ኩንታል እህል ፣ 775 ኩንታል ዘይት ፣ 2,440 ኩንታል አልሚ ምግብና 2,325 ኩንታል ጥራጥ ይገኙበታል።

መንግሥት ቀደም ሲል ከተባባሪዎቹ ጋር በመሆን አራት አጥኚ ቡድን በመላክ በሱማሌ ክልል ካደረገው መደበኛ ጥናትና ከምግብ አቅርቦቱ በተጨማሪ በአሁኑ ጊዜ የክልሉን አብዛኛዎቹን ዞኖች ያዳረሰውንና በርካታ ወገኖች ለምግብ እጥረት ካጋለጠው ድርቅ አኳያ ለክልሉ የሚቀርበው አስቸኳይ የምግብ ዕርዳታ አቅርቦት ለተረጂዎች የሚከፋፈልበትን ሁኔታ የሚያስተባብሩና የሰውና የእንስሳት ጤና ፣የውሃና የግጦሽ ሁኔታን እና ለሌሎችም ከችግሩ ጋር ተዛማጅ ጉዳዮች በቅርብ እየተከታተሉ ለሚወሰዱ እርምጃዎች ሪፖርት የሚያደርጉ የተለያዩ ሙያተኞችን ያካተተ አራት ቡድኖች በክልሉ ተመድበዋል። ከአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ፣ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ፣ ከግብርና እና ከሚመለከታቸው መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የተውጣጡ ባለሙያዎች በአባልነት የሚገኙባቸው እነዚሁ አራት ተንቀሳቃሽ ቡድኖች ጅጅጋ ፣ጎዴ ፣ ሊበን እና አፍዴር ዞኖች ላይ በመሆን ሁኔታዎችን በቅርበት እየተከታተሉ በተሽከርካሪ ላይ በተገጠመው ተንቀሳቃሽ የግንኙነት ሬዮ አማካይነት በየአካባቢው ስላለው አጠቃላይ የዕለት ተዕለት ሁኔታ ለማዕከል በሚያቀርቡት ሪፖርትና ቀደም ሲል ከተካሄደው የመደበኛ ጥናት ውጤት ላይ በመመሥረት መንግሥት ተከታታይ እርምጃዎችን በመውሰድ ላይ ይገኛል።

## በበጀት ዓመቱ ከ400 በላይ ለሚሆኑ ባለሙያዎች ሥልጠና ተሰጠ

በ1997 በጀት ዓመት በፌዴራል አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ አማካይነት በተዘጋጁ ልዩ ልዩ ሥልጠናዎች ከክልልና ከፌዴራል አካላት የተውጣጡ 452 ባለሙያዎች መካፈላቸው ተመለከተ።

ይህ የተመለከተው ኤጀንሲው በ1997 በጀት ዓመት ያከናወናቸውን ዋና ዋና ተግባራት በዋናው የዓመቱ የሥራ ክንውን ሪፖርት ላይ ሲሆን ፣ በሪፖርቱ እንደተብራራው የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሥራን ለማጠናከር እንዲረዳ

> የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሥራን ለማጠናከር እንዲረዳ በሥርዓተ ምግብ ጥናት በቅድሚያ ማስጠ ንቀቂያ ዳታ አተረጓገምና አተናተን በመረጃ አያያዝና አሰባሰብ ለ162 የክልልና የማዕከል የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ባለሙያዎች ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡

በሥርዓተ ምግብ ጥናት በቅድሚያ ማስጠ ንቀቂያ ዳታ አተረጓገምና አተናተን በመረጃ አያያዝና አሰባሰብ ለ162 የክልልና የማዕከል የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ባለሙያዎች ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓትን በኤጀንሲው ውስጥ ለማስፈን እንዲቻል 110 ለሚሆኑ የኤጀንሲው ባለሙያዎች በኢንተርኔትና በኮምፒውተር አጠቃቀም ሥልጠና ላይ እንዲካፈሉ ተደርጓል፡፡ ለ54 ሴቶችና 81 ወንዶች በአጠቃላይ ለ135 ሠራተኞች በሥርዓተ ፆታና ሥነተዋልዶ ዙሪያ የግንዛቤ ማዳበሪያ ሥልጠና መስጠቱን ያመለከተው ሰነዱ በመንግሥት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች በሥራ አመራር በውጤት ተኮር እና በዕቅድ አፈጻጸም መመሪያ ላይ ግንዛቤ የሚያስጨብጥ አውደጥናት ለ45 የበላይ የሥራ ሃላፊዎች እንደተሰጠም ተመልክቷል፡፡



## በብር 245.6 ሺህ እህልና ቁሳቁስ ከአገር ውስጥ ግዥ ተከናውኗል

በ1998 በጀት ዓመት ባለፉት 6 ወራት ውስጥ ለምግብ እጥረት ተጋልጠው ዕርዳታ ያስፈልጋቸዋል ለተባሉ ተረጂዎች በብር 61 ሺህ 106 እህልና አልሚ ምግብ ፣ በብር 184 ሺህ 497 ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች ማለትም 5 ሺ የኘላስቲክ ከረጢቶችና 20 ሺ ኩባያና ሣህኖች በድምሩ በብር 245 ሺህ 603 ከ37 ሳንቲም ከአገር ውስጥ ተገዝቶ ለተጎጂ ወገኖች ተከፋፍሏል፡፡ ባለፉት ስድስት ወራት ከማዕከላዊ መጋዘኖች ወደ ክልሎች 122 ሺ 132 ሜትሪክ ቶን እህል ተጓጉዟል፡፡

በኤጀንሲው መጋዘን ውስጥ የሚገኘውን እህል በጥራት ለመያዝ በተደረገው እንቅስቃሴ 42 ሺ 718 ሜትሪክ ቶን እህል ደህንነቱ ተጠብቆ ለተገቢው አገልግሎት እንዲውል ተደርጓል፡፡

## የናሙና የጥናት ኘሮጀክቱ ነባሩን የአደጋ ተጋላጭነት ደረጃ አጠናን ስልት ለማሻሻል ያስችላል ተባለ

በአደጋ መከላከልና ዝግጅነት ኤጀንሲ እና በአሜሪካን ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅት /ዩኤስ.ኤ.አይዲ/ ትብብር በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የተካሄደው በህብረተሰቡ የገቢ ምንጭ ትንተና ላይ የተመሠረተ መነሻ ናሙና የጥናት ኘሮጀክት ለአደጋ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች ያለውን ሁኔታ ለማወቅና አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ ይደረግ የነበረውን ነባር የአጠናን ዘዴ ለማሻሻል እንደሚረዳ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ሲሞን መቻለ ገለፁ፡፡

ዋና ዳይሬክተሩ ይኸንን የገለፁት ታህሳስ 7 ቀን 1998 ዓ.ም የናሙና ጥናት ኘሮጀክቱ ውጤት



አዲሱ የአጠናን ስልት ለጥናቱ የሚያስፈልገውን የሰው ኃይልና ገንዘብ ጨምሮ በጥናቱ የሚደረስበትን ውጤት ተአማኒነትንም ለማሻሻል እገዛ ያደርጋል የሚል ተስፋ አለ፡፡

ለሚመለከታቸው መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በቀረበበት ወቅት ነው፡፡ዋና ዳይሬ ክተሩ ቀደም ሲል አደጋን ከመከላከል ጋር የተያያዙ ጥናቶችን ለማካሄድ ያስፈልግ የነበረው የሰው ሀይልና ገንዘብ በርካታ እንደሆነ አመልክተው አዲሱ የአጠናን ስልት ለጥናቱ የሚያስፈልገውን የሰው ኃይልና ገንዘብ ጨምሮ በጥናቱ የሚደረስበትን ውጤት ተአማኒነትንም



ለማሻሻል እገዛ ያደርጋል የሚል ተስፋ አለን ብለዋል፡፡ በማያያዝም ከናሙና የጥናት ኘሮጀክቱ የሚገኘው ውጤት በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት የሚያገኝ ከሆነ ነባሩን የአደጋ ተጋላጭነት አጠናን ዘዴ በመተካት በሌሎች ክልሎችም ተግባራዊ እንደሚሆን ገልፀዋል፡፡ በዚህ ሒደት ሌሎች አጋር ድርጅቶችም ተሳታፊ ይሆናሉ የሚል ተስፋ አለን ያሉት ዋና ዳይሬክተር ሲሞን ለዚህ ናሙና ጥናት አስፈላጊውን የሰው ሀይልና የገንዘብ ድጋፍ ያደረጉትን የአሜሪካን ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅትንና ሌሎችንም አመስግነዋል፡፡

የጥናት ኘሮጀክት ውጤቱ በቀረበበት ለግማሽ ቀን የቆየ ዐውደ ጥናት ላይ እንደተገለፀው የዚህ ናሙና ጥናት ዋነኛ ዓላማ ለአደጋ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች የሚደረገውን የዕርዳታ ፍላጎት አጠናን ስልት ማሻሻል ሲሆን የአዲሱ አጠናን ዘዴ ዋነኛ መሠረትም የአደጋ ተጋላጭ አካባቢዎች ነዋሪያችን የገቢ ምንጮችን የሚመለከቱ መረጃዎችን ማሰባሰብና በዛ ላይ የተመሠረተ ትንተና ማካሔድ ነው፡፡ በዚህ ሂደትም የገቢ ምንጭ መረጃዎች የሚሠበሰቡት በቡድን ሳይሆን

በቤተሰብ ደረጃ መሆኑ ይኸን የአጠናን ዘዴ ለየት የሚያደርገው መሆኑ በዐውደ ጥናቱ ላይ ተገልጿል፡፡

ከዚህም በላይ በዚህ የጥናት ኘሮጀክት ከአደጋ ተጋላጭነት ጋር በተያያዘ የሚጠኑትን አካባቢዎች በአየር ሁኔታ /ቆላ ፣ ደጋ እና ወይና አጋ/ ፣ በነዋሪዎቹ የሀብት ደረጃ /ደሀ ፣ በጣም ደሀ ፣ መካከለኛ እና የተሻሉ/ እንዲሁም በመሠረታዊ የአኗኗር ሁኔታ በመከፋፈልና ከነዚህ የተለያዩ ክፍሎች የሚገኙትን ከገቢ ምንጭ ጋር የተያያዙ መረጃዎች በተናጠል በመተንተን በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ውስጥ ለሚካሄዱት የአደጋ ተጋላጭነት ጥናቶች መነሻ /ቤዝላይን/ የሚሆን መሠረት ለማስቀመጥ ጥረት ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት በቀጣይ የአደጋ ተጋላጭነት ጥናቶች የሚያጋጥሙትን ሁኔታዎች በመነሻነት ከተቀመጠው ጋር በማነፃፀር አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል የመፍትሔ ሀሳብ ለማቅረብ እንደሚቻል በአውደ ጥናቱ ላይ ተመልክቷል፡፡

የጥናቱን አነሳስ ፣ አካሄድና አሁን የተደረሰበትን ደረጃ ግንዛቤ ለማስጨበጥ የሚያስችሉ ማብራሪያዎች በዐውደ ጥናቱ አዘጋጆች ከቀረቡ በኋላ ከተሳታፊዎቹ በቀረቡ ጥያቄዎችና አስተያየቶች ዙሪያ ሰፊ ውይይት ተደርጓል፡፡

በዚህ ዐውደ ጥናት ላይ ጉዳዩ ከመሚመለከታቸው የተለያዩ መንግሥታዊና እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የተውጣጡ 40 የሚሆኑ ባለሙያዎች ተሳታፊ መሆናቸው ታውቋል፡፡